# ሃይማኖት ውስጥ በመወሸቅ  የከሰረ ፖለቲካን ማስታመም ይቻላል?

ዘአማን  በላይ   bzaman@yahoo.com

አንድ ቆየት ያለና ተደጋግሞ የሚወሳ አባባል አለ – "ያስብከው ዓላማ አልሳካ ብሎህ ሃሳብህ ሲጠጥር፤ ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር" የሚል፡፡ ይህ ብሂል አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ቀደም ሲል አልሞት አልሆንልህ ያለው የዓላማ ሃሳብ ማጣፊያው ሲያጥረው፣ ጠንካራውን ጉዳይ ለማሳካት በቅራቢያው የሚገኘውን ለስላሳ እሳቤን ማጦዝ እንዳለበት  የሚያስረዳ ነው፡፡

ታዲያ ለእንዲህ ዓይነቱ ግለሰብም ይሁን ቡድን የጡዘቱ የልኬት መጠን ያሻውን ያህል ቢሆን  ደንታው አይደለም፡፡  ዓላማው ለማሳካት "ጠጣሩን ይወጥሩልኛል"  ያላቸውን  የጎንዮሽ ስንካላ እውነታዎችን በተሸመደመደ ሁኔታ ውስጥም ሆኖ ቢሆን፤ በሴራ ንድፈ - ሃሳብ  (Conspiracy theory) እየለወሰ ያሻውን ከመዘላበድ ወደ ኋላ አይልም፡፡

ጉዳዩ የእርሱን ውሽልሽል አመክንዩ እስካሳካለት ድረሰም የድርጊቱ የውል  ቋጠሮ  ህዝብን የሚጎዳና የሀገር ጠንቅ እንኳን ቢሆን እርሱ ምን ተዳው?!... ብቻ ምክሮ ያልተሳካለትን ጠጣር እውነት፣ በጊዜያዊ ችግሮች አማካኝነት ሊያሳካ ካለበት ቦታ ሆኖ "ጉሮ ወሸባዬ"  በማለት  የህልም ዓለም "ኮሜዲ ድራማውን" ይከውናል፤ አሊያም ያስከውናል፡፡... እርግጥም እንዲህ ያለውን አስገራሚ ራስን የማታለል ድርጊትን ሳይሆን አይቀርም– የሀገራችን አርሶ አደር "በልጅ አመካኝቶ፣ ይበሏል አንጉቶ"  በማለት የሚሳለቀው ፡፡

ማንኛውም የዚህ መጣጥፍ አንባቢ የጽሑፌ  አስኳል  ጉዳይ ቀደም ሲል  በመግቢያዬ ላይ የጠቀስኩትን ይትብሃል   ለመተንተን አለመሆኑን እንደሚገነዘብልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ አባባሉን ያነሳሁት ግን ያለምክንያት አይደለም፡፡ ለምን ቢሉ፤ የይትብሃሉ ፍሬ ሃሳብ የሆነውና ያልተሳካን "ጠጣር ሃቅን"  ትቶ የራሱ  ያልሆነውን  "የላላ ጉዳይን"  የመወጠሩ  ተምሳሌታዊ አብነት እና ሃይማኖትን እንደ መወሸቂያ የቆጠሩት በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ የተቃውሞ ጎራ ፖለቲከኞች ጋር አንድና አንድ ስለሆኑብኝ ነው – "ስልቻም ቀልቀሎ፤ ቀልቀሎም ስልቻ"  እንደሚባለው ዓይነት፡፡

እርግጥ እነዚህ በተቃዋሚነት የተሰለፉ ግለሰቦችና  ቡድኖች  በአንድ ወቅት የደርግ "ካኪ ለባሽ"  የነበሩ፣ በሀገራችን ውስጥ ለአራት ጊዜያት በተካሄዱ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ  ምርጫዎች በህዝቡ ካርድ የተተፉ እንዲሁም ሀገራችን በአሸበሪነት የሰየመቻቸው ቡድኖች አባላትና እነርሱን ተክተው የሚናውዙ ተዋናዮች ስብስብ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ የስብስቡ ዓላማ አንድ ነው፡፡ ይኸውም የፖለቲካ ኪሳራ ህመማቸውን ሃይማኖት ውስጥ ተወሽቀው በማራመድ ከውድቃታቸው ለማገገም "የመላላጥ" አባዜ ነው፡፡ ገሚሱ ባህር ማዶ ቁጭ ብሎ በጋዜጠኝነት ሽፋን ሀገር ውስጥ ያለውን ነባራዊ እውነታ እያጣመመ በማቅረብ ያመረቀዘ የሽንፈት ቁስሉን

የሚሸር እየመሰለው ማንነታቸው የማይታወቁ ግለሰቦችን በመጥቀስ አሉባልታዎችን ያናፍሳል፡፡ ራሱ በጎነጎነው ሸውራራ እሳቤም እንደ እብድ ብቻውን ይስቃል፡፡

ሌላኛው የከሰሩ ፖለቲከኞች ፅንፍ ደግሞ "ከጥንት ጀምሮ ስናየው የኖርነው፣ ሲነድ ሲቃጠል የሚስቅ እሳት ነው" ከሚለው አባባል ውስጥ "እሳትን" ወደ "ኢሳት" ቀይሮ የአለቃውን የዶክተር ብርሃኑ ነጋን የሞተ አጀንዳን ለማስፈጸም የሚማስነው የባህር ማዶ የቅጥፈት መቀመሪያ ጣቢያ ነው፡፡

ከዚህ ጣቢያ ጋር እጅና ጓንት ሆነው የሚሰሩትና ከሃይማኖታዊ ድንጋጌዎች ወጥተው በፖለቲካኝነት የተሰለፉት በስደት የሚገኘው የኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን አባላቶችም አሜሪካ ውስጥ የእነ ግንቦት ሰባት ተወርዋሪ ድንጋይ ሆነው ማገልገል ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡፡ ምንም እንኳን ለእነዚህ አባቶች ምድራዊ ስልጣን ለምን እንዳስፈለጋቸው ግልጽ ባይሆንም፣ሃይማኖታዊ ካባቸውን ለብሰው ለሚያገለግሏቸው የሽብር ቡድኑ አባላት ግን እጅግ ዘግናኝ እና አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ "የምፅዓት ቀን ጀግና" ለመባል የሚሹ ሳይሆኑ የሚቀሩ አይመስሉኝም፡፡ … ምናልባትም "ምፅዓተ ሽብር" የሚባል ቀን ካለ ማለቴ ነው፡፡

እነዚህ ጥቅል እውነታዎች የሚያመለክቱን ነገር ቢኖር፣ በአሁኑ ወቅት ሁሉም የከሰረ ፖለቲካ አጀንዳ አራማጆች ከምርጫ ውጭ ስልጣን ለመያዝ አስፍስፈውለት የነበሩትን "ጠጣር ፖለቲካ" ለማላላት ማቄን ጨርቄን ሳይሉ ሃይማኖት ውስጥ መወሸቃቸውን ነው፡፡ ታዲያ እኔም ለውድ አንባቢዎቼ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ "ሃይማኖት ውስጥ ወሽቅ የከሰረ ፖለቲካ ማገገም የቻላልን?" የሚል ጥያቄን በማንሳት፣ በእነዚህ "ሀገራዊ ጉዶች" ቁርኝት አማካኝነት የሚካሄዱ ወፍ ዘራሽ አሉባልታዎችን እንዲሁም በኢትዮጵያ ህዝብ ሀብትና ንብረት ላይ የሚያካሂዱትን ሰሞነኛ የሴራ ዱለታን እየነቀስኩ ለማብራራት እሞክራለሁ፡፡

በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ሊፈጠር የሚችልን አንድን ክስተት በመምዘዝ የከሰረ ፖለቲካቸውን ለማስታመም ከሚሞክሩትና በተቀናጀ ሁኔታ የኢትዮጵያን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ጥቅሞች በማጣጣል ላይ ያነጣጠሩት እነዚህ "እኔ ከምትኩ ሰርዶ አይብቀል" ባዮች፣ ከመሰንበታቸው በዘመቻ መልክ በሙስሊሙ ምርጫ ላይ እና በዋልድባ ገዳም ጉዳይ የቅጥፈት አታሞአቸውን ሲደልቁ ሰንብተዋል፡፡ አስደላቂዎቹ ደግሞ አሸባሪው ግንቦት ሰባት እና ኢሳት የሚባለው የቡድኑ ማላዘኛ ጣቢያ ናቸው፡፡

ድለቃውን በመርዝ ቃላት እየቀመረ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁከትና ብጥብጥ እንዲነግስ ከሚሹ ጣቢያዎች ውስጥ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ (በዋነኛነት የአማርኛው ክፍል ) አንዱ ነው፡፡ ግብዓት መሬቱ ከተፈጸመ ሁለት አስርታትን በዘለለው የደርግ ሥርዓት እንዲሁም የሙት ዓለም ፖለቲካ በነበረው ኢህአፓ ውስጥ ሁነኛ ባለሚል መሆናቸው በይፋ የሚነገርላቸው "ጋዜጠኛ ፖለቲከኞች"፣ የትናንት ሽንፈታቸውን ዛሬ ላይ "በአሉባልታ" ለመወጣት በሚመስል መልኩ እጅግ የሚያስገርም አዲስ "የሙስሊም ምርጫን" ሹክሹክታ ይዘው ብቅ ብለዋል፡፡

ከጀርባቸው የራሳቸው የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸውን ሰዎች አነፍንፈው በማነጋገር (ተጠያቂዎቹ እነርሱ ይሁኑ፣ አይሁኑ ማንም እርግጠኛ በማይሆንበት ሁኔታ) "መንግስት በየቀበሌው፣ በየክፍለ ከተማው የበወረዳው ባሉት

መዋቅሮቹ አማካኝነት የሙስሊሙን ምርጫ ሊያካሂድ ነው…” የሚል መሰረተ - ቢስ አሉባልታዎችን በማሰራጨት በሀገራችን ውስጥ ሠላም እንዳይኖር ሲተጉ ነበር፡፡

ምንም እንኳን ጣቢያው ውስጥ ያሉት የቀድሞው ሥርዓት ቅሪቶችና የከሰመው ኢህአፓ ርዝራዦች ዓላማቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱት የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ዕድገቶችን በማጥላላት እንዲስተጓጎሉ ማድረግ ቢሆንም፤ ይህ ከንቱ የጥፋት ተስፋቸው ላለፉት 21 ዓመታት እንዳልተሳካው ሁሉ፣ ህልማቸው ከለሊት ቅዥትነት (night mare) የሚዘል ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በቅጥፈት ወሬ እና “በአሉባልታ ናዳ” የፈረሰ ወይም የሚፈርስ ማህበረሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ የሌለ በመሆኑ ነው፡፡

ሆኖም ሙስሊም ማህበረሰብ ያቀረበው ትክክለኛና ተገቢ የሆነ የመብት ጥያቄ ከምርጫ አኳያ መንግስት እጁን የሚያስገባበት አንዳችም ምክንያት የሌለው መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በሀገር ውስጥ ራሳቸውን “የሙስሊሙ ጥያቄ አስተባባሪዎች ነን” እያሉ ከኋላቸው በከሰሩ ፖለቲከኞች የሚመሩት ግለሰቦችም ይሁኑ “ሳያጣሩ ወሬ፣ ሳይገድሉ ጎፈሬ” እንደሚባለው ሃላፊነት በጎደለው ሁኔታ ውዥንብር የሚነዛው የአሜሪካ ድምጽ አማርኛው ክፍል፤ ቢያንስ እየጎመዘዛቸውም ቢሆን ህገ - መንግስቱ ላይ ስለሰፈረው ስለ ሃይማኖትና መንግስት መለያየት ምስጢር አንብበው ቢሆን ማወቅ ያላባቸው ይመስለኛል፡፡

ህገ - መንግስቱን በማስከበር የዜጎችን መሰረታዊ ጥቅሞች በመጠበቅ ተግባር ላይ የተሰማራው የኢፌዴሪ መንግስት፤ እንኳንስ በሃይማኖታዊ ምርጫ ጉዳይ እጁን ሊያስገባ ቀርቶ፣ የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ በሚደረጉ ምርጫዎችም ቢሆኑ የሀገሪቱን ህዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አክብሮ የሚንቀሳቀስና በተዓማኒነት እንዲፈጸሙ በጽናትና በቁርጠኝነት ኃላፊነቱን ሲወጣ የነበረ ሃይል ነው፡፡

ሌላው ቢቀር መንግስት በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ ከገባ፤ የዴሞክራሲ መሰረታዊ መርሆ የሆነው የእምነት ነጻነት ይሸራረፋል፡፡ የእምነት እኩልነትም አብሮ ይጣሳል፡፡ ይህም ዴሞክራሲ በሀገራችን እንዳይገነባ ማነቆ መሆኑ አይቀርም፡፡ ታዲያ መንግስት ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ስር እንዲሰድ እየፈለገ፣ እንደመን መልሶ ራሱ ህገ - መንግስቱን ይጥሳል ተብሎ ይታሰባል?– እንዲያው በተገኘው የአጀንዳ አጋጣሚ ሁሉ” እሪ፣ እምባ” ለማለት ካልተፈለገ በስተቀር፡፡

እርግጥ ነገሩ “ሌባ እናት ልጇን አታምንም” እንደሚባለው ሁሉ፤ የራሳቸውን የጋዜጠኝነት ሥነ - ምግባር ከሚዛናዊነት አኳያ እየደፈጠጡ የግንቦት ሰባት ተላላኪ በመሆን ለሚያገለግሉት የአሜሪካ ድምጽ የከሰሩ ፖለቲከኛ ጋዜጠኞች “መንግስት የሙስሊሙን ምርጫ ሊያካሂድ ነው…” ቢሉ አይፈረድባቸውም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ነገር እንደ ራሳቸው ስነ-ምግባር የጎደለው ተግባር ስለሚመስላቸው ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ግን መቼም ቢሆን፤ ከራሱ የሥነ - ምግባር አሰራሮች ጋር ተጋጭቶ አያውቅም– አመጣጡም ሆነ ባህሪው እንዲህ እንዲያደርግ አይፈቅዱለትምና፡፡

እዚህ ላይ የሙስሊሙን የምርጫ ጥያቄ በተመለከተ ውሳኙ ሙስሊሙ ማህበረሰብ እንጂ፤ መንግስት አለመሆኑን በሰው አጀንዳ ሙሾ የሚያወርዱት “ተመራጭ ነን” የሚሉ ወገኖችን የዋሽንግተኖቹ የውሸት ጋዜጠኞች (Pseudo journalists) ማወቅ አለባቸው፡፡ ለነገሩ አብዛኛው የሙስሊም ምዕመን ‘ምርጫው

በርካታ አማኞችን እንዲያሳትፍልን በመንግስት መዋቅሮች አማካኝነት ይፈጸምልን' ካለ መብቱ ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ 'ምርጫው መካሄድ ያለበት በመስጊድ ነው' ካለም ይህም ማንም የማይገስሰው ዴሞክራሲያዊ መብቱ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተረፈ መንግስት 'ምርጫህን እዚህ አድርግ፣ አታድርግ' የማለት መብት ሆነ አሰራር የለውም– ህገ - መንግስቱ ይገድበዋልና፡፡

ይሁን እንጂ እነ ቪኦኤ የግንቦት ሰባት ድራማ ተዋናይ ሆነው የሌለ ነገርን በምናባቸው እያቀናበሩ ቢለፍፉም፣ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ያለማንም ጣልቃ ገብነት (የመንግስትም ይሁን የውጭ ኃይሎች) የሚያካሂደው ምርጫ ሰላማዊ መሆኑን የማረጋገጥ ህገ -መንግስታዊ ግዴታ ያለበት መሆኑን ቢገነዘቡ እሰየው ነው፡፡ በመሆኑም የእነርሱ ሰላምን የማደፍረስ "ቅንጅታዊ ድራማ" ግቡን እንዳይመታ መንግስትና ሰላም ወዳዱ ሙስሊም ምዕመን በንቃት እየተከታተሏቸው መሆናቸውን ሊያውቁት ይገባል፡፡

ውድ አንባቢዎቼ! የከሰሩ ፖለቲከኞችን በአንድ ዓይነት ሃይማኖታዊ ጥላ ስር እንዲወሽቁ ያደረጋቸው ሌላኛው ጉዳይ፣ መንግስት የሀገሪቱን ልማት ለማፋጠን ከዋልድባ ገዳም በርካታ ኪሎ ሜትሮች ያህል የሚርቀውና በቅዱስ ገዳሙ ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ የማያደርሰው የስኳር ፋብሪካ ነው፡፡ ታዲያ የፋብሪካውን ግንባታ ተከትሎ 'ታሪካዊው ገዳም ሊፈርስ ነው' በሚል በዘመቻ መልክ በተካሄደ አሉባልታ ያልተሳተፈ ቀቢጸ ተሰፈኛ አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡

አዎ! እርግጥም እንዲህ ዓይነቱ ጸያፍ አስተሳሰብ በምርጫ 97 ወቅት የቅንጅት ነውጠኛ አመራሮች ሲጠቀሙበት ነበር፡፡ በወቅቱም በውጭ የሚኖረው ሲኖዶስ አባቶች ሰላምን የሚባርኩባትን መስቀላቸውን የአመጽ መቀስቀሻና ቡራኬ መስጫ አድርገውት በአሜሪካ ጎዳናዎች በቀስቃሽነት ተሰልፈው መፈክር ሲያሰሙበት ነበር፡፡

'የመጀመሪያው ሥነ - ፍጥረት አዳም፣ በምድር ላይ እስካለህ ድረስ ጥረህ ግረህ ብላ ተብሏል፣ እናንተም እንዲሁ አድርጉ' ብለው ማስተማር የሚገባቸው የውጭው ሲኖዶስ የሃይማኖት አባቶች፣ ከሃይማኖታቸው አስተምህሮት ባፈነገጠ ሁኔታ የአሸባሪዎችን አጀንዳ በይፋ ማራመዳቸው በእጅጉ ዘግናኝ ነው፡፡ እርግጥ ማንም ሰው ቢሆን መንግስትን ሊቃወም ይችላል፡፡ መብቱም ነው፡፡ ዳሩ ግን መንግስትና ህዝብን በማይለይ ሁኔታ "የኢትዮጵያን ህዝብ ንብረት አትጠቀሙ" እያሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ አመጽን ማቀጣጠል እንኳንስ 'በሃይማኖታዊ አባትነት ቆመናል' ከሚሉ ወገኖች ቀርቶ ከአንድ ተራ ምዕመንም ቢሆን የሚጠበቅ አይደለም፡፡

እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ምናልባት የተፈጠሩ ጊዜያዊ ችግሮች ካሉ መንግስትን ይተቻል እንጂ፣ የሽብር ሃይሎችን አጀንዳ በባንዳነት አንግቦ በህዝብ ጥቅም ላይ አያሚርትም፡፡ እናም በዋልድባ ገዳም ላይ ያልተደረገውን እንደተፈጸመ አድርጎ ማውራት ከህዝቦች ጠላት ጋር በማበር የሀገራችንን ልማት ለማደናቀፍ ከሚደረግ ሴራ በስተቀር ሌላ ትርጉም አይሰጠውም፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ "የሽብር ምጽዓት ቀን አርበኞች" ለመሆን በመውተርተር ላይ የሚገኙት እነዚህ በሃይማኖት ሽፋን ፖለቲካዊ አጀንዳቸውን የሚያራግቡትን አባት ተብዬዎች፣ እንደምን የህዝብ ጠላት ሊሆኑ

እንደሚችሉ ለማናችንም ግልጽ አይደለም፡፡ ለነገሩ በስደት የሚገኘው ሲኖዶስ አባቶች ግንቦት ሰባት መራሽ አጀንዳን ተከትለው በተሳሳተ አቅጣጫ እንደ ቦይ ውኃ ቢፈሱም፤ የዚህ ጽሑፍ አንባቢ ማንኛውም ሃይማኖት መቼም ቢሆን የግጭት መንስዔ ሊሆን እንደማይችል መገንዘቡ አይቀርም፡፡

እንደሚታወቀው ክርስትና፣ እስልምናም ሆኑ ሌሎች ሃይማኖቶች መርሃቸው ሰላምንና ፍቅርን እንዲሁም ትዕግትንና መቻቻል መሰረት አድርገው አስምህሮታቸውን ያከናውናሉ፡፡ ከዚህ ውጭ የትኛውም ሃይማኖት ጥላቻና ግጭትን የሚሰብክና የሚቀሰቅስ ይዘት የለውም፡፡ ታዲያ ስደተኛውን ሲኖዶስ እንመራዋለን የሚሉት ውጭ የሚኖሩ አባቶች ዓላማቸው ከቶ ምን ሊባል ይችላል?— በፀረ-ህገ መንግስታዊነት ተሰልፈው የህዝቡን መሰረታዊ ጥቅሞች በሽብርተኞች እየተነዱ ለመቦጫጨር ካልፈለጉ በስተቀር፡፡

ያም ሆነ ይህ፤ በሃይማኖት ስም የሚንቀሳቀሱና በውስጡ ተወሽቀው የገበያ ግርግር ለመፍጠር የሚሹ የከሰሩ ፖለቲከኞችን፤ ለብጥብጥ መፍጠሪያ በሽፋንነት ለሚጠቀሙበት ሃይማኖት አንዳችም ክብር የሌላቸው መሆኑን በስደት የሚገኙት የኦርቶዶክስ ሲኖዶስ አባቶች ሁነኛ አስረጅ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ምዕመናን ከፈጣሪያቸው ጋር የሚያገናኛቸውን ሃይማኖት ለፖለቲካ ዓላማ ማራመጃ ሽፋን አድርጎ በቀጥታ መሳሪያነት መጠቀም "አባቶቹ" ለህዝበ ምዕመናኑም ይሁን ለፈጣሪያቸው ደንታ ቢስ እንዲሁም ክብር የለሽ መሆናቸውን በማያሻማ ሁኔታ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ነው፡፡ ለምን ቢሉ፤ እንኳንስ የሃይማኖት አባቶች ነን የሚሉ ግለሰቦች ቀርቶ፤ ሃይማኖቱን የሚያከብር አንድ ሰውም ቢሆን በሃይማኖት ስም ወንጀል ለመፈጸም ፈጽሞ ይንቀሳቀሳል ተብሎ ስለማይታሰብ ነው፡፡

ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ በሃይማኖት ውስጥ ተወሽቆ ፖለቲካዊ ፍላጎትን ለማሳካት የሚደረግ በቀቢጸ - ተስፋ የመንገራገጭ አባዜ ከሰሞነኛው የሙስሊሙ ምዕመን ምርጫ ጋርም ከበስተጀርባ ሆኖ እየተተወነበት ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ትክክለኛውን የሙስሊሙን ማህበረሰብ ፍላጎት በአየር ላይ በመጥለፍ በምርጫው ሰበብ ሁከት እንዲፈጠር የሚሹት ግለሰቦች ማንነታቸውን ለማወቅ የተለየ ጥበብ የሚጠይቅ አይመስለኝም፡፡

እርግጥም የጥፋት ተዋናዩቹ ግንቦት ሰባት እና ኢሳት ከኋላ ሆነው የሚገፋፏቸው የከሰሩ ፖለቲከኞች ናቸው፡ ፡ እነዚህ ኪሳራን በየጊዜው ማወራረድ የማይሰለቻቸው ሽብርተኞች በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ውድድር የሽንፈትን ፅዋ በተደጋጋሚ ያነሱ ሲሆን፤ ሰላማዊ ምህዳርን እንደ ተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ ከሩቁ የሚሸሹ ለመሆናቸው እስካሁን ድረስ ባህር ማዶ ቁጭ ብለው "ዘራፍ እኛ የአመጽ አሽከሮች" በማለት በምናብ ዓለም የሚቧችሩት ያልሰመረ ህልማቸው አመላካች ነው፡፡

የአመጽ ሙከራቸው በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት የተቀናጀ ጥረት ሲከሽፍ፣ ዛሬ ላይ ሆነው ሃይማኖቶችን መጠጊያ በማድረግና በዚህም ሳቢያ የሚፈጠር ግጭትን እንደ አንድ መታገያ ስልት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ለዚህም ነው — አንዴ የሙስሊሙን ማህብረሰብ ፍትህዊ ጥያቄዎች የራሳቸው አጀንዳ አድርገው፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በዋልድባ ገዳም ላይ ያልተፈጸመን ተግባር ከመሰሎዎቻቸው ሚዲያዎች ጋር በመተባበር እያራገቡ ሀገራዊ ሠላም እንዳይኖር ሌት ተቀን በመራወጥ ላይ የሚገኙት፡፡

መንግስት የሙስሊሙን ትክክለኛ ጥያቄዎች ህገ - መንግስቱን መሰረት አድርጎ የማያዳግም ምላሽ ሲሰጥ የሃፍረት ካባ ለብሰው ከሚለፍፉበት ሚዲያ ተጠራርገር የጠፉት እነዚህ ኃይሎች፤ ዛሬ ደግሞ ከምርጫው በስተጀርባ ሆነው የለመዱትን የውሸት ወሬ ቀምረው የመንግትን ህገ-መንግስታዊ አሰራር ለማደናቀፍ የፈጠራ ዲስኩርን እያራገቡ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ዕድገት ስለማይመኙም ደርሰው የገዳማትና የአድባራት ተቆርቋሪዎች በመምሰል ተረት - ተረት በማነብነብና በማስነብነብ እነሆ በቁራ ጩኸት የከሰረ ፖለቲካቸውን ማስታመም እንደ ልክፍት እየደጋገሙት ነው።

ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ የ“ላም አለኝ በሰማይ…” ቅዠት የሚቻልበት ተጨባጭ ሁኔታ በዓለም አቀፍ ደረጃ በልማታዊ ተምሳሌትነት በምትጠቀሰው ሀገራችን ውስጥ የማይታሰብ መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ ምክንያቱም የአዲስቷ ኢትዮጵያ ህገ - መንግስታዊ ስርዓት ለሃይማኖትም ይሁን እርሱን ተከትለው ለሚከሰቱ የግጭት “ህልማዊ ሁነቶች” ማስተናገጃ ቦታ የሌለው በመሆኑ ነው፡፡ ቸር እንሰንብት።